# ጠበንጃውን ሰጥቶ ስለ ጀበርናው ማውራት አይበጅም

የኢትዮ-ኤርትራ ካሳ ኮሚሽን በሁለቱ አገሮች መካከል የተደረገውን ጦርነት ተከትሎ ስለደረሰው ጉዳት አንዱ ለሌላው መክፈል ስልሚገባው ካሳ ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ. ም. ውሳኔውን ይፋ አድርጓል፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በበነጋው ነሐሴ 12 ቀን 2001 ዓ.ም፤ የመንግስት ኮሙኑኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ደግሞ ነሐሴ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በዚሁ ጉዳይ ላይ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ መግለጫዎቹ ባንድ በኩል "ሙሉውን ሰነድ አጥንተን የመንግስትን አቋም እናሳውቃለን" ሲሉ በሌላ በኩል ደግሞ ኤርትራ ለኢትዮጵያ የምትከፍለው ካሳ መጠን የዐሥር ሚልዮን ዶላር ብልጫ ያለው መሆኑን በመጥቀስ ሊያፅናኑን ዳድቷቸዋል፡፡

ይህም ኾኖ የዛሬዎቹ መግለጫዎች ሚያዝያ 13 ቀን 1994 ዓ.ም የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ አስመልክቶ በአቶ ስዩም መስፍን ከተሰጠው መግለጫ ይሻላሉ፡፡ ቢያንስ "በጦር ሜዳ የተገኘው ድላችን በችሎትም ተደገመ፤" "የእኛ የሆነው ባድመ እና አካባቢው ብቻ ሳይኾን በጾረና አካባቢ በኤርትራ እጅ የነበረ መሬትም ተጨምሮልናል፣ ደስ ይበላችኹ፤ ደስታችኹንም በአደባባይ ለመግለጽ ትችላላችኹ" ይሉት ቧልት ነገር በሶሞኑ መግለጫዎች አልታየም፡፡ እንደዛሬው "ሰነዱን አጥንተን ዝርዝር አቋማችንን እናሳውቃለን" በማለት ፈንታ ያኔ "ውሳኔውን አናከብራለን፣ የሄጉን ኮሚሽንንም እናደንቃለን" ነበር የተባለው፡፡ ብዙም ሳይቆይ ተገኘ የተባለው ድል ሐሰት መኾኑ፣ በሕዝብ እና በመከላከያ ሰራዊታችን ዘንድም ፈጽሞ ተቀባይነት እንደማይኖረው ሲታወቅ "ውሳኔውን አንቀበልም" የሚል ደብዳቤ በወቅቱ የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ ለነበሩት ለኮፊ አናን ተጻፈላቸው፤ አድናቆት የተቸረው ኮሚሽንም ባላንጣ ከኾነው ሻዕብያ ባልተናነሰ ደረጃ የፕሮፓጋንዳ ዒላማ ኾነ፡፡

በመሠረቱ ኢትዮጵያ በሄጉ ክርክር ለመረታቷ ተጠያቂው ኢህአዴግ ራሱ እንጂ ኮሚሽኑ አይደለም፡፡ ስህተቱ ወደ ሄግ በመኬዱ፣ በዳኞቹ መረጣ፣ በጠበቆች ቅጥር ወይም ሂደቱን በሚገባ ካለመከታተል እና ካለመምራት የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡ በየትኛውም ረገድ ቢኾንም ተጠያቂነቱ ከኢህአዴግ ውጪ አይደለም፡፡ ኢህአዴግ ለምን ይህ ሆነ ብሎ ራሱን ለመመርመር ድፍረቱ ሲያጣ መጀመርያ ሽንፈቱን እንደ ድል አድረጎ ሊያቀርብ ሞከረ፡፡ ይህ ሲጋለጥበት ድግሞ ራሱ ያቋቋመውን ችሎት በባለጋራነት ፈርጆ የጠላሁትን ጥሉልኝ ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብን መቀስቀስ ጀመረ፡፡ ኢህአዴግ ስህተትን ወደ ሌላ ማስፈንጠር እንጂ ወደ ውስጥ ጠልቆ በመግባት ራስን መመርመር አይሆንለትም፡፡

የካሳ ኮሚሽኑን አስመልክቶ የተሰጡት መግለጫዎች የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ተከትሎ ከተሰጠው መግለጫ አንጻር የአቀራረብ ልዩነት ቢኖራቸውም የባሕርይ ልዩነት ግን የላቸውም፡፡ ሁለቱም መግለጫዎች አጽንኦት ሰጥተው የደጋገሙት ጉዳይ ወራሪው የኤርትራ መንግስት እንደ ኾነ መረጋገጡን፣ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ስለኤርትራ መንግስት ጠብ ጫሪነት ግንዛቤ እያገኘ መሄዱን እና የተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ም/ቤት በዚህ መንግስት ላይ ማዕቀብ ስለመጣል በውይይት ላይ መኾኑን ነው፡፡

እነዚህ ጉዳዮች እውነት ቢሆኑም አሁን ከተሰጠው የኮሚሽኑ ውሳኔ ጋር ተያይዘው መነሳት ያለባቸው ጉዳዮች ግን አይደሉም፡፡ በምትኩ ወራሪው የሻዕብያ መንግስት መሆኑ እየታወቀ በካሳ ኮሚሽኑ ውሳኔ ውስጥ ለምን ሳይንጸባረቅ ቀረ? በምፅዋና አሰብ ወደቦች ላይ የነበረው እና በሻዕብያ የተዘረፈው የዜጎች እና የመንግስት ሃብት ስለምን በካሳ ዝርዝር ውስጥ ሳይገባ ታለፈ? ...ወዘተ የመሳሰሉት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ቁምነገሩ የካሳ ጉዳይ ኾኖ እያለ ስለኤርትራ ወራሪነት እና ሊጣልባት ስለሚገባው ማዕቀብ መናገር የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ኢህአዴግ አሁንም ከተጠያቂነት ለመሸሽ እንዲያመቸው ተኩረታችን በሌላ ጉዳይ ላይ እንዲተከል እየሞከረ መኾኑን ነው፡፡

የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ሌላ ነው፤ አንድን ሥራ መርቶ ውጤት ማምጣት ደግሞ የተለየ ነው፡፡ ሁለቱ ተግባራት ተያያዥነት ቢኖራቸውም ለየቅል መኾናቸው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ብቃት ያለው አመራር ሰጥቶ የሃገርን ጥቅም በማስጠበቅና የወገንን ፍላጎት ዳር በማድረስ ላይ የተመሠረተ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አገርን እና ወገን ለተጨማሪ ስኬት እንዲነሣሱ የኀይል መሠረትት ይኾናል፡፡ በተጨባጭ በስኬት ላይ ያልተመሠረተ የሕዝብ ግንኙነት ስራ ግን ሐሰት እና ማጨበርበር ብቻ ነው ሊኾን የሚችለው፤ ውጤቱም የመሪዎች ተአማኒነት መሸርሸር፣ የዜጎች በመሪዎቻቸው

ማፈር፣ ዜግነታዊ ስሜታቸው መጎዳት ነው፡፡ የሕዝብ ግንኙነት ስራ በምንም ተኣምር የአመራር ብቃትን አይተካም፡፡

የኤርትራ መንግስት አገራችንን ወረረ፡፡ በሰላም ልቀቅ ተብሎ እምቢ ቢል በሕዝባችን እና በሰራዊታችን የተባበረ ትግል ወረራውን ለመቀልበስ ተችሏል፡፡ የኢህአዴግ የተሐድሶ አመራር ግን በጦር ሜዳ የተገኘውን ድል በሄጉ ክርክር ሳያስጠበቀው ቀርቷል፡፡ በተፃራሪው የኤርትራ መንግስት በጦር ሜዳ የደረሰበትን ውርደት ለመቀልበስ በእልኸ እና በጽናት በመስራቱ ሄግ ላይ ያገኘው ውጤት መጽናኛ ኾኖለታል፡፡ የኤርትራ መንግስት ወራሪው እሱ መኾኑን በበየነበት የካሳ ኮሚሽን ፊት ጥርሱን ነክሶ በመከራከሩ ሊደርስበት ይችል ከነበረው ተደራራቢ ጉዳት ራሱን አትርፏል፡፡ በአንጻሩ ይህ እውነታ አገራችን ኢትዮጵያ የሚመራት አካል ወርድ እና ቁመት የሚያመለክት ይመስለኛል፡፡

ለዋና ጸሐፊ ኮፊ አናን የተላከው የ"አንቀበልም" ደብዳቤ የተጻፈበት ቀለም ሳይደርቅ ኢህአዴግ በኅዳር 1996 ዓ.ም. ለፓርላማው፤ "የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ በመርሕ ደረጃ እንቀበላለን፤ አፈጻጸሙን በሚመለከት ግን በሁለቱም መንግስታት መካከል ድርድር እንዲኖር እንፈልጋለን" የሚል ውሳኔ እንዲተላለፍ ተደረገ፡፡ የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ በመርሕ ደረጃ ከተቀበሉ በኂላ "ውሳኔው አንድ መንደር ሳይሆን አንድን ቤት ለሁለት የሚከፍል ውሳኔ ስለሆነ ይህንን ለማስቀረት እንደራደር" ብሎ የክርክር መቅድም ማቅረብ ወደ እውነተኛ መፍትሔ የሚያደርስ አይኾንም፡፡ ሐሳቡ ለሁለተኛ ጊዜ የታየ "ቀኝ ኂላ ዙር" እርምጃ ከመሆኑ ባሻገር በይዘቱም ጠመንጃውን አስረክቦ ስለ ጀበርናው እንደመከራከር ይቆጠራል፡፡

ባድመን ለሻዕብያ መስጠት ወራሪው የሻዕብያ መንግስት ለሠራው አጠፌ ሥራ ሽልማት እንደመስጠት ይቆጠራል፡፡ የሻዕብያን መሪ ዓምባገነን አገዛዝ የሚያፈረጥም፣ ለኤርትራም የማይበጅ፣ በሁለቱም ሃገሮች እና ሕዝቦች መካከል የሰከነ እና ዘለቄታዊ ግንኙነት እንዳይሰፍን ሳንካ የሚፈጥር እርምጃ ነው፡፡ ይብሱን የአካባቢውን ሰላም ሊያውክ የሚችል እርምጃ ሊሆን ይችላል፡፡

በየኅዳሩ የፓርላማ ውሎ የተሰማው ሌላው አስገራሚው ንግግር ለሻዕብያ መሪዎች የቀረበላቸው የ"እኛ እንሻላችኂለን" መለማመጥ ነው፡፡ "እኛ የኤርትራን ነፃነት ያለማወላወል የተቀበልን፣ በዚህም ሰበብ ብዙ ፖለቲካ ዋጋ የከፈልን ሰዎች እያለን ድርድሩን ብተቀበሉ ይሻላችኂል፣ የኤርትራን ነፃነት ከማይቀበሉት፣ የኢትዮጵያ  የባሕር በር ..... ከሚሉት ተቃዋሚዎች ይልቅ እኛ እንሻላችኂለን" የሚል ይዘት ያለው መልእክት ነበር ከፓርላማው አደራሽ የተላለፈላቸው፡፡ አነጋገሩ ከፓርላማው አደራሽ ውጪም ቢሆን  አንዳንድ የኢህአዴግ መሪዎች፡- "አሁንም ቢሆን ለኤርትራ ነፃነት እንታገላለን" በማለት ሲደጋግሙት ተደምጠዋል፡፡ እንዲህም ተብሎ ግን የሻዕብያው መሪ ከያዘው አቋም ፍንክች የሚል ኾኖ አልተገኘም፡፡ እርሱ እንደኾነ "እኔ ያልኩት ካልኾነ የመቶ ዓመት የቤት ሥራ እሰጣችኂለሁ" እያለ ነው፤ በተግባር መሞከሩም አልቀረም፡፡ ሰውዬው የውኃ-ልኩን የማወቅ ችግር አለበት፡፡ ባደመን በወረራ እንደያዘ፤ "የኤርትራ ሰራዊት ከባድመ ወጣ ማለት የፀሐይ መጥለቅያ ምዕራብ መሆኑ ቀርቶ ምስራቅ ሆነ ማለት ነው" ማለቱን እናስታውስለታለን፡፡

የኢትዮ-ኤርትራ ችግር የመቶ ዓመት ታሪክ ያለው ችግር እንደ መኾኑ የመቶ ዓመት የቤት ሥራ ነው ቢባልለት አይገርመኝም፡፡ የሻዕብያው መሪ "ለኢትዮጵያ የመቶ ዓመት የቤት ሥራ እሰጣታለሁ" ማለቱ "በሁከት የተሞላ የመቶ ዓመት የቤት ሥራ አሰጣታለሁ" ማለቱ እንደኾነ ግልጽ ነው፡፡ ይህን ደግሞ ሌላ ዓለም ላይ ተቀምጦ ሊያደርገው ይችል እንደ ኾነ እንጂ ከመረብ ማዶ አፍንጫችን ሥር ተቀምጦ ሊያደርገው ግን ከቶ አይቻለውም፡፡ በበኩሌ ለኤርትራ የመቶ ዓመት የሁከት የቤት ስራ አልመኝላትም፡፡ ኢትዮጵያውያንም ኾኑ ኤርትራውያን ስለ የመቶ ዓመት የቤት ስራ ማሰብ ካለብን የቤት ሥራው ሁለቱንም አገሮች እና ሕዝቦች ስለማቀራረብ እና አንድ ስለማድረግ እንጂ አንዱ ሌላውን ሰለማወክ መሆን የለበትም፡፡

መነጋገር መደራደር መቀራረብ ይገባናል፡፡ መነጋገሩ እና መደራደሩ ግን ስልጀበርናው መሆን የለበትም፡፡ ድርድሩ የባህር በርን፣ ድንበርን፣ የኤሌክትክ ሃይልን፣ ውሃን ይዞ ለጉሮሮና ለልማት በቂ ዋስትና ስለመፍጠርን እና የመሳሰሉትን የሁለታችንን ህልውና በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ሁሉን አቀፍ ድርድር መኾን አለበት፡፡ ድርድሩ ተፈጥሯዊ እና ታሪካዊ ትስስራችን የተገነዘበ፣ ለሁለቱ ወገኖች ስጋት እና ጥቅም ተገቢውን ስፍራ የሚሰጥ መኾን ይኖርበታል፡፡ ድርድሩ ከሁለቱ መሪዎች የስልጣን ስሌት ውጪ የኾነ፣ ይልቁንስ የሁለቱን ሕዝቦች ጥቅም እና ትስስር ላይ ያነጣጠረ መኾን

ይገባዋል። ድርድሩ አፈናን እና የሰብአዊ መብት ጥሰትን አስወግዶ የዴሞክራሲ እና ሕገ መንግስታዊነት ዕሴቶችን በመገንባት የአካባቢያችንን አሳፋሪ ገበና ስለመሸፈን መኾን ይኖርበታል።

ስየ አብርሃ

ነሐሴ 21ቀን 2001 ዓ.ም.

.....................

seabrag@gmail.com ላይ እገኛለሁ